**የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዌስት ሚድላንድስ ዩናይትድ ኪንግደም የቀብር መረዳጃ አገልግሎት መተዳደሪያ ደንብ**

**ምዕራፍ 1**

**ጠቅላላ ድንጋጌ**

**አንቀጽ 1.1 አድራሻና ባለቤትነት**

1.1.1 የቀብር መረዳጃ አገልግሎቱ የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዌስት ሚድላንድስ ያቋቋመው ነው። በመሆኑም አገልግሎቱ ማህበሩ ያዘጋጀውና ባለቤት የሆነበት ተቋም ሆኖ ይታወቃል።

1.1.2 አገልግሎቱ ለትርፍ የማይሰራ የመረዳጃ ሕብረት ነው።

1.1.3 የኢትዮጵያውይን ማሕበር በዌስት ሚድላንድስ አድራሻ የአገልግሎቱ አድራሻ ይሆናል።

1.1.4 አገልግሎቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው።

**አንቀጽ 1.2 ዓላማው**

1.2.1 የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዌስት ሚድላንድስ ዩናይትድ ኪንግደም የቀብር መረዳጃ አገልግሎት ማሕበሩ በሚያወጣው መስፈርት መሠረትነት ለዚህ አገልግሎት የተመዘገበና የአገልግሎቱን ወርሃዊ ክፍያ የሚከፍል አባል ወይም የተመዘገበ ልጅ ("የተመዘገበ ልጅ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ 2.2.6 ን ያመሳክሩ) በሞት ሲለይ ለቀብር ስነ - ስርዓት ማስፈጸሚያ ወይም ለአስከሬን መላኪያ የሚሆን የገንዘብ እርዳታ ማድረግ፣

1.2.2 ለአገልግሎቱ የተመዘገበ አባል ወይም የአባል ቤተሰብ ሲሞት የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዌስት ሚድላንድስ ዩናይትድ ኪንግደም የቀብር ዋስትና አገልግሎት አባላት ለቅሶ እንዲደርሱና እንዲያስተዛዝኑ፣ ማሳወቅና ማስተባበር፣

1.2.3 ለቀብር አፈጻጸም ወይም ለአስከሬን ማጓጓዝ አስፈላጊ የሆኑ ምክሮችን ለሟች ቤተሰብ መስጠት፣

1.2.4 ለወደፊት "ለአባላት ይጠቅማል" ብሎ የሚያምንበትን ማንኛውንም ዓላማ እንደ አስፈላጊነቱ መጨመር።

**አንቀጽ 1.3 ትርጓሜ**

1.3.1 በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴትም ያገለግላል።
1.3.2 "የቀብር መረዳጃ አገልግሎት" ማለት የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዌስት ሚድላንድስ ዩናይትድ ኪንግደም የቀብር መረዳጃ አገልግሎት ማለት ነው።

1.3.3 "አባል" ማለት የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዌስት ሚዳንድስ ዩናይትድ ኪንግደም የቀብር መረዳጃ አገልግሎት መተዳደሪያን ደንብ ተቀብሎ የተመዘገበ እና የአባልነት ግዳጁን የፈጸመ ማለት ነው።

1.3.4 ቤተሰብ ማለት በአገልግሎቱ አባል ስር የሚተዳደሩ እድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ማለት ነው።

**አንቀጽ 1.4 የ"የቀብር መረዳጃ አገልግሎት" ገቢ**

1.4.1 ከአባልነት ክፍያ

-ከእያንዳንዱ አባል የመመዝገቢያ £75 እና የወርሃዊ £5 ክፍያ
-ከእያንዳንዱ ዕድሜው ከ21 አመት በታች የሆነ የአባል ልጅ የወርሃዊ £2.50 ክፍያ፤
-1.4.2 በስጦታ ከሚገኝ፤
-1.4.2 ስፓንሰር ከሚያደርጉ ወይም ከሚረዱ ድርጅቶች ይሆናል።

**ምዕራፍ 2**

**አባልነት**

**አንቀጽ 2.1 አባል ስለመሆን**

2.1.1 በዌስት ሚድላንድስ ዩናይትድ ኪንግደም የሚኖር ዕድሜው 21 እና ከዚያ በላይ የሆነ፣

2.1.2 የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዌስት ሚድላንድስ ዩናይትድ ኪንግደም የቀብር መረዳጃ አገልግሎት ደንብን የተቀበለ፣

2.1.3 ከአካባቢው ውጪ ባለ በሌላ (ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ) ቦታ የሚኖር ዕድሜው ከ21 ዓመት በላይ የሆነ እና (ኢትዮጵያዊ እና ወይም ትውልደ ኢትዮጵያ) አባል ለመሆን የሚጠበቅበትን የሚያሟላ።

**አንቅጽ 2.2 የአባል መብት፣**

2.2.1 አንድ አባል በአባልነት ተመዝግቦና የወር ክፍያ ግዴታውን አሟልቶ ስድስት ወር (6 ወር) ካልሞላው ሞት ቢያጋጥም የገንዘብ እርዳታ አይከፈልበትም። ነገር ግን ሐዘን ቢደርስበት የአገልግሎቱ አባላት ለማስተዛዘን አብረውት ይሆናሉ፡፡

2.2.2 የአባልነት ግዴታውን ማለትም የዓመታዊ ክፍያውን በሶስት ወር ያጠናቀቀ እና ወርሃዊ ክፍያውን በሙሉ የከፈለ አባል ቢያልፍ ሦስት ሺህ ፓውንድ (£3,000) ወጪ ይደረግለታል፡፡ ይህ አይነቱ አባልም "አዲስ" ተብሎ ይለያል፡፡

2.2.3 አገልግሎቱ የገንዘብ አቅሙ ሲጠነክር አባላት ያላቸውን ቆይታ መሠረት ያደረገ የሐዘን ወቅት ዕርዳታ መሻሻል ያደርጋል። ይኸውም የዕርዳታ ክፍያው አምስት ሺህ ፓውንድ (£5,000) ይሆናል። ይህ አይነቱ አባልም "ነባር" ተብሎ ይለያል፡፡ ይህ የዕርዳታ ገንዘብ ለውጥ ተግባራዊ የሚሆነው የአገልግሎቱ የገንዘብ አቅም መጠንከር በአመራሩ ከታመነበትና የአፈፃፀም ሥርአት ከተዘጋጀለት እንዲሁም ለአባላት በግልፅ ይፋ ከተደረገ በኖላ ይሆናል።

2.2.4 ይህ ከላይ (በ2.2.2 እና በ2.2.3 ላይ) የተቀመጠውና ማንኛውም የአባሉ ልጅ የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆነው ከወላጁ ወቅታዊ የአባልነት መልክ ጋር በተመሳሰለ መንገድ ነው፡፡

2.2.5 የአባል ልጅ ሃያ አንድ ዓመት (21) በሞላው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የዓመቱን ክፍያ በመክፈል እራሱን ችሎ አባል ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሳይሆን ቢቀር ልጁ አገልግሎት የሚያገኝበትን ግዴታ እንዳልተወጣ ተቆጥሮ አገልግሎቱ ይቆማል። ሕብረቱም የተለመደውን የ£2.50 የወር ክፍያ አይቀበልም። ለብቻው እንደ አባል የሚጠበቅበትን አሟልቶ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮም ሙሉ አባል እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

2.2.6 አባል የሆነው ሰው በሞት ቢያልፍ በልጅነት ተመዝግበው ያሉ የድርሻቸውን በመክፈል (£2.50) እስከ እድሜአቸው ገደብ ድረስ ይቆያሉ። ይህንን ማድረግ የማይችሉበት ሁኔታ ካለ ማህበሩ ልጆቹን ያለ ክፍያ ባለመብትነታቸው እንዲቆዩ ያደርጋል።

## አንቀጽ 2.3 የአባል ግዴታ

2.3.1 የቀብር መረዳጃ አገልግሎት ደንቡ የሚጠይቀውን መፈጸም።

2.3.2 የአባልነትና ሌሎች ቅጾችንም በአግባቡ በትክክል ሞልቶ ለዋስትና አገልግሎቱ መስጠት።

2.3.3 መደበኛ የአባልነት መመዝገቢያና የወር መዋጮዎችን በወቅቱ መክፈል።

2.3.4 አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠም በስተቀር በጠቅላላ ስበሰባ ላይ መገኘት።

2.3.5 በአባላት መካከል የመግባባትና የመተባበር ስሜት እንዲዳብር መርዳት።

2.3.6 አባል ወይም የአባል ቤተሰብ በሞት በተለየ ጊዜ ቤተሰብን ለማስተዛዘንና ለመቅበር አሊያም አስክሬን ለመሸኘት በሚኖሩ ሥነ-ሥርአቶች ላይ መገኘት::

2.3.7 አባል ወይም የአባል ቤተሰብ (የተመዘገበ ልጅ) በሞት ከተለየ፣ ጉዳዩን ለዋስትና አገልግሎቱ ተጠሪ ማሳወቅ።

2.3.8 የአባል ወይም የአባል ቤተሰብ ሁኔታ ከተለወጠ፣ ለምሳሌ የልጅ እድሜ ከ21 አመት በላይ ከሆነ ለውጥ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለዋስትና አገልግሎቱ ማሳወቅ::

2.3.9 በተጨማሪም በቤተሰብ ውስጥ ተጨማሪ አዲስ ልጅ ከተወለደ ወይም ከ21 ዓመት በታች የሆነ የአባል ልጅ ከኢትዮጵያ ወይም ከሌላ ሥፍራ ከመጣ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ልጅ ተገቢውን ክፍያ በመክፈል አባልነት ማስመዝገብ::
2.3.10 አዲስ የተወለደ ሕፃን ልጅ በተወለደ በ1ወር ጊዜ ውስጥ አባል ወላጆቹ ሊያስመዘግቡት ይገባል:: በዚህ የ1ወር ጊዜ ውስጥ የሞት አደጋ ቢፈጠርበት ቤተሰቡ የአንድን አባል ግማሽ እርዳታ ይቀበላል (የአዲስ አባል ዕርዳታ ለውጥ እስካልተደረገበት ድረስ £1,500 ይሆናል)።ይህ የዕርዳታ ገንዘብ መጠን በተጠቀሰው ጊዜ ተመዝግቦ ለተገኘ እስከ 6 ወር ላለ አዲስ የተወለደ ሕፃን ተመሳሳይ ይሆናል::

### ምዕ ራ ፍ 3

### አንቀጽ 3.1 የሥነ ሥርዓት እርምጃ

3.1.1 አንድ አባል “ክፍያውን አላሟላም” የሚባለው የሦስት ወር ክፍያ ሳይከፍል ከቀረ ነው፡፡ በተከታታይ ለሦስት ወራት ሳይከፍል የቆይ አባል £20.00 ተቀጥቶ ውዝፍ ክፍያውን እንዲያጠናቅቅ ይጠበቅበታል። ይህ የቅጣት ተመን ከሦስት ወር በኋላ በየወሩ £5.00 የሚጨምር ሲሆን 6 ወር ላይ ሲደርስ ከአባልነት ይሰናበታል::

3.1.2 የአባልነት ክፍያውን ላላሟላ አባል የስልክ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ከአባልነት ሲሰናበትም እንዲሁ በስልክ ይገለፅለታል። አንቀፅ 2.3.3. ይመልከቱ፡፡

3.1.3 አንድ አባል ለረጅም ጊዜ ከአገር (UK) ውጭ የሚቆይ ከሆነ ቅድመ ክፍያ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የአባልነት መብቱም ተጠብቆ ይቆያል።

3.1.4 አገልግሎቱ የተቋቋመበትን አላማ የሚፈፅመው (ገንዘብ የሚከፍለው) አገር ውስጥ (ዩኬ ውስጥ ብቻ ነው)። ይህም ማለት የቀብር መረዳጃው ገንዘብ በተቋሙ ወደሌላ አገር አያዘዋውርም።

3.1.5 የአባልነት ግዴታውን ባለመክፈሉ የተሰናበተ አባል እንደ አዲስ ሊመዘገብ ይችላል። የአባልነት መብቱም እንደ ማንኛውም አዲስ አባል ይሆናል።

3.1.6 አንድ አባል የሐሰት መረጃ ለአገልግሎቱ ከሰጠና በዚህም የሃሰት መረጃ ምክንያት ሊሰጠው የማይገባውን ገንዘብም ይሁን ሌላ ጥቅም ለማግኘት ጥረት ሲያደርግ ከተገኘ እና ከተረጋገጠ፣ የዋስትና አገልግሎቱ አባልነቱን ሊሰርዝ ይችላል። ያገኘውም ጥቅም ካለ፣ እንዲመልስ በህግ ይጠይቀዋል።

3.1.7 አንድ አባል በ3.1.6 ምክንያትነት ከአባልነት ቢገለል አባል በነበረበት ወቅት ለአገልግሎቱ የከፈለው ማንኛውም ገንዘብ አይመለስለትም።

3.1.8 በ3.1.6 ላይ በተጠቀሰው ምክንያት ከአገልግሎቱ የተገለለውን አባል፣ የዋስትና አገልግሎቱ ሁለተኛ በአባልነት አይቀበለውም፡፡

**አንቀፅ 4**

**4.1 ማሳሰቢያ**

4.1.1 ተደጋጋሚ ሞት ቢደርስና የአገልሎቱን አቅም ቢያዳክመው የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዌስት ሚድላንድስ አባላትን የገንዘብ እርዳታ እንዲያደርጉና የአገልግሎቱን አቅም እንዲያበረቱ ይጠይቃል፡፡

4.1.2 በየትኛውም የሞት አደጋ ላይ አገልግሎቱ የሞት ምስክር ወይም ሌላ ሕጋዊ ወረቀት ማረጋገጫን ይጠይቃል-ኮፒውንም ያስቀራል::

4.1.3 አንድ አባል ከጠፋ ወይም የት እንደደረሰ የማይታወቅ ከሆነ፣ በአባሉ ስም ከአገልግሎቱ የገንዘብ ክፍያ አይጠየቅበትም ::

4.1.4 ለሕክምና ወይም ለሌላ ምክንያት የዋስትና አገልግሎቱ ክፍያ አያደርግም፡:

**አንቀጽ 5**

**አገልግሎቱን ስለማፍርስ**

5.1 የዋስትና አገልግሎቱን ለማፍረስ የጠቅላላ አባላቱ ሁለት ሶስተኛው (2/3) ድምጽ ያስፈልጋል።

5.2 የዋስትና አገልግሎቱ የፈረሰ እንደሆነ፣ የአገልግሎቱ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ ጥሬ ገንዘብ ጭምር ለየኢትዮጵያውያን ማህበር በዌስት ሚድላንድስ (Ethiopian Community in West Midlands) እንዲሰጥ ይደረጋል።

ማስታወሻ:- የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዌስት ሚድላንድስ ዩናይትድ ኪንግደም የቀብር ዋስትና አገልግሎት አመታዊ የስራ አፈፃፀም እና የሒሳብ አያያዝ በየአመቱ January 1st የሚጀምር ሲሆን የዓመቱ ሒሳብ በ December 31st ይዘጋል:: February ላይም ከጠቅላላ የአባላት ስብሰባ ጋር አንድ ላይ ስብሰባ ይደረግበታል።